የኢ/እ/ጉ/ጠ/ም/ቤት
የፌደራል ምርጫ አስፈጻሚ ቦርድ

የኢ/እ/ጉ/ጠ/ም/ቤት ምርጫ አፈጻጸም ማንዋል ስልጠና

ምርጫ ለጽኑ ተቋማዊ ና እስላማዊ አንድነት ማንባታ!

to add notes

የስልጠናው ሰነድ ይዘት

1. መግቢያ
2. ስለምርጫ ምንነት
3. ስለምርጫ አስፈላጊነትና ጥቅሞች
4. የምርጫ አፈጻጸም ዋና ዋና መርሆዎች
5. የመራጭነትና ዕጩ ተመራጮች መስፈርት
6. የምርጫ ስራ ተግባራት ምእራፎች

4.1. **ቅድመ-ምርጫ ምእራፍ**

4.2. **የምርጫ ትግበራ ምእራፍ**

- የመስጅድ ደረጃ ምርጫ
- የወረዳ ምርጫ
- የዞን/ ክ/ከተማ ምርጫ
- የክልል/ከተማ ምርጫ
- የፊደራል መጅሊስ ምርጫ

4.3. **የድህረ ምርጫ ምእራፍ**

መግቢያ

- መጅሊስ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የጋራ አሰባሳቢ ተቋም በመሆን የሙስሊሙን ማ/ሰብ በእኩልነት፤ በፍትሃዊነት፤ በአቃፊነትና በአካታችነት በማገልግል ሀይማኖቱ በነፃነት የሚተገብርበትንና የሚስፋፋበትን ሁኔታ ለማመቻቸት በአባቶች ትግል ተቋቁሞ በኢፌድሪ አዋጅ ቁጥር 1207/2012 ህጋዊ ሰውነት ያገኘ መሆኑ የታወቃል።

- ከላይ የተገለጸውን አላማ ለመሳካት የመላውን ህዝበ-ሙስሊም ተሳትፎና ውክልና በሚያረጋግጥ አኳሃን ነጻና ፍትሃዊ የምርጫ ስርኣትን ተከትሎ የተቋሙን አመራር ምርጫ ማካሄድ ግድ ይሆናል።

- ጠቅላይ ምክር ቤቱ ላለፉት ዓመታት ካሳለፈው የለውጥና ማሻሻያ ሂደት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄደውን የመጅሊስ አመራር አካላት ምርጫ ሂደት ለመምራት የምርጫ አስፈጻሚ ቦርድ ከፍተኛ ሀገራዊና ዲናዊ ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ፣

መግቢያ.... የቀጠለ

- ቦርዱ የምርጫ ሂደቱን በመጅሊሱ የህግ ሰውነት አዋጅ ቁጥር 1207፣ በሕገ-መጅሊሱ እንዲሁም በመጅሊሱ ጠቅላላ ጉባዔ በጸደቀው የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መከናወኑን ማረጋገጥ ያለበት በመሆኑ፣

- ምርጫው በሚከናወንባቸው ከመስጂድ ጀምሮ እስካ ፌዴራል ደረጃ ያሉ ማእከላት የምርጫ ዝግጅትና አተገባበር ሂደቶችን በቀላሉ ለመረዳትና ለመተግበር የሚያስችል የአሰራር መግለጫ (ማኑዋል) ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

- የምርጫ አስፈጻሚ ቦርዱ ይህንን የምርጫ አሰራር መግለጫ (ማኑዋል) ሰነድ አዘጋጅቷል።

1. የምርጫ ምንነት

ምርጫ፦ ማለት በየደረጃው ያሉ የመጅሊስ መዋቅሮች ውስጥ በተለያየ ደረጃ የሚሳተፉ የመጅሊስ አመራር አካላት የሚመረጡበት የተሳትፎና ውክልና ማረጋገጫ ሂደት ነው::

(የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 005/2017፣ አንቀፅ 2 — 2)

2. የምርጫ አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ

1. ሁሉንም አሳታፊ የሆነ ምርጫ ማካሄድ የመጅሊስን አስተዳደር ከሱፊ-ሰለፊ የመዝሀብ እና ጀመኣ ልዩነት ዉዝግብ ቅኝት በማውጣት መጅሊሱን በየዘርፉ ሕዝበ ሙስሊሙን *በእኩልነት፣ በፍትሀዊነት፣ በአቃፊነትና አካታችነት ወደሚያገለግል ተቋም ለማሸጋገር እና ለማጽናት ያግዛል።*

2. መጅሊሱን ለመምራት አደራ የሚረከቡት ተወካዮች በአስተዳደራዊ ብቃትና *በዲናዊ ሰነምግባር የላቁ ሰዎች* ህዝብ ሙስሊሙ *በራሱ ፍላጎት ለይቶ እንዲመርጥ* እድል የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር መጅሊሱን ለመምራት የተመርጡትንም ተጣያቂነት ለማስፈን ያግዛል።

3. በየዘርፉ በሚደረግ ምርጫ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የኔ የሚላቸውን ተወካዮቹን በማስመረጡ የመጅሊሱን የሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች *የጋራ ወኪልነትና ቅቡልነቱን ለማሳደግ በእጅጉ ይረዳል።*

የምርጫ.... የቀጠለ

4. ምርጫው ህዝበ ሙስሊሙን በመስጂድ ደርጃ በየዘርፉ መደራጀት አስገዳጅ ስለሚያደርግ መስጂዶች የየራሳቸውን አባላትን መዝገቦ ለማወቅ እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ መቀበል ስለሚያስችላቸው ለራሳቸውና *ለመጅሊስ የገቢ ምንጭ ማስገኛ እድልን ይፈጥራል።*

5. የምርጫ ምዝገባ የየመስጂዱን ጀመዓ አባላት ብዛት የየወረዳውን የየዞኑን የየክልልና በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የሙስሊሞችን ትክክለኛ ቁጥር በውል ለይቶ ለማወቅ በር ስለሚከፍት ወደፊት ተገቢውን *የልማት እቅድ ለማውጣት ትልቅ እድል ይከፍታል።*

3.የምርጫ አተገባበር መርሆዎች

1. አካታችና ህዝባዊ ተሳትፎ
2. ከወገንተኝነት የጸዳ ምርጫ
3. ነጻ እና ፍትሃዊ ምርጫ
4. ሁሉን አቀፍ ምርጫ
5. መስጅድን ማእከል ያደረገ ምርጫ

4. የመራጭነት መመዘኛዎች

1. ማንኛውም ከ18 ዓመት በላይ የሆነና በመኖሪያው አካባቢ የሚገኝ መስጂድ ተጠቃሚ የሆነ ወይም መስጂድ አልባ አካባቢ የሚኖርና ለመራጭነት የተመዘገበ ሙስሊም ኢትዮጵያዊ፣
2. አባል በሆነበት መስጂድ ጀምኣ ወይም በሚሳተፍበት የምርጫ ጣቢያ አካባቢ የሚኖርና ማንነቱን የሚገልጽ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፋይዳ ካርድ ማቅረብ የሚችል።

5. የዕጩ ተመራጮች መስፈርት

በሁሉም እርከን በተመራጭነት የሚሳተፍ እጩ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ሊያሟላ ይገባል፡፡

1. ኢትዮጵያዊ መስሊም ሆኖ በሚወዳደርበት የምርጫ ጣቢያ አካባቢ ነዋሪ የሆነ፤
2. የሚኖርበትን ክልል ቋንቋ መስማትና መናገር የሚችል፤
3. ህዝበ መስሊሙን ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ፣
4. የመስሊሙን ማህበረሰብ ጎብረት፣ አንድነት እና ትብብር ላይ ጽኑ ዕምነት ያለው፤
5. የእስልምና ህግጋትን የሚያከብርና ሀይማኖታዊ ተግባራቱን በቋሚነት የሚፈጽም፤
6. ለኢሰላምና ለመስሊሞች ባለው ታማኝነትና ለአሏህ ያለው ፍራቻ በተግባሩና ግልፅነት ባላቸው የሸሪዓዊ ህግ መመዘኛዎች የተረጋገጠ፤
7. በየትኛውም የመጅሊስ እርከን ላይ በኃላፊነት ተቀምጦ በስነምግባር ችግር ያልተሰናበተ ወይም ከፍተኛ የዲሲፕሊን እርምጃ አግባብነት ባለው አካል ያልተወሰደበት፤

የዕጩ....የቀጠለ

8. የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አመራርና የመንግስት የፖለቲካ ተሿሚ ያልሆነ፣
10. ዑለማን ሳይጨምር ለራሱም ሆነ ለቤተሰቡ ቋሚ ገቢ ያለው ለመሆኑ ማስመስከር የሚችል፤
11. ለወጣቶች አደረጃጀት በሌሎች አደረጃጀቶች ውስጥም የመወዳደር መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ እድሜያቸው ከ18-35 የሆኑ ሰዎች፣
12. ከወረዳ እስከ ፌዴራል መጅሊስ ለጠቅላላ ጉባኤ አባልነት በዑለማ ም/ቤቱ የሚወከሉ የዑለማ ም/ቤት አባላት ምልመላና መስፈርት በዑለማ ጉባዔው መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

7. የምርጫ አይነቶች

የማህበራዊ አደረጃጀት የዘርፍ ተወካዮች የውክልና ምርጫ፦

1. የኡለማኦች ዘርፍ - (ኡለማኦች፤ኢማሞችና ዱኣቶች)
2. የምሁራን ዘርፍ ምርጫ (ቢያንስ የመጀመሪያ የት/ት ዝግጅት ያለው/ያላት)
3. የወጣቶች ዘርፍ ምርጫ (ከ18-38 አመት እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወንዶችና ሴቶች)
4. የሴቶች ዘርፍ ምርጫ (በጾታ ሴት ሆና ከ18 አመት እድሜ ጀምሮ)
5. የሰራተኛው ማህበረሰብ ዘርፍ ምርጫ (ባለሀብት፥ የቅጥር ሰራትኛ፤ አርብቶ አደር፤ ገበሬ፤ ልዩ ልዩ ሙያተኛ)

በየአስተዳደር እርከኖች የሚደርግ የውክልና ምርጫ ዓይነቶች፤

1. በየመስጂዱ ለወረዳ መጅሊስ ተወካይነት የሚደረግ ምርጫ፣
2. በወረዳ መጅሊስ ም/ቤት የወረዳ ስራ አስፈጻሚ፤ እና የስራ አመራር አባላት ምርጫ
3. በዞን/ክ/ከተማ መጅሊስ ም/ቤት የዞን/ክ/ከተማ ስራ አስፈጻሚ፤ እና የስራ አመራር አባላት ምርጫ
4. በክልል (ከተማ አስተዳደር) መጅሊስ ም/ቤት የክልል/ከተማ ስራ አስፈጻሚ እና የስራ አመራር አባላት ምርጫ
5. በፌደራል ጠ/ም/ቤት የፌደራል መጅሊስ ስራ አስፈጻሚ እና የስራ አመራር አባላት ምርጫ

8. የምርጫ ዑድቶች

8.1 የቅድመ ምርጫ ምእራፍ ተግባራት

ቅድመ ምርጫ ምዕራፍ በየደረጃው የሚከናወኑ የምርጫ ሂደቶች ከመከናወናቸው በፊት ለምርጫው ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቅ የሚገባቸውን ተግባራት ያካትታል። እነዚህም ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

- ከምርጫ መጀመር በፊት በሁሉም በሀገሪቷ ክፍል የሚገኙ ወረዳ መጅሊስ አካላት በያንዳንዱ መስጂድ ***አባላትን በዘርፍ በመለየት መመዝገብ***
  - ***መረጃ ማደራጀት***፦ የመራጭ ብዛት እና ሌሎች መረጃዎችን ማሰባሰብ
  - በያንዳንዱ መስጅድ የሚገኙ አባላት ከሚከተሉት ዘርፍ በመረጡት አደረጃጀት መመዝገብ
    1) በዓሊሞች እና ዳኢዎች ዘርፍ፣
    2) በምሁራን ዘርፍ
    2) በባለሀብቶች እና ልዩ ልዩ ባለሙያዎች ዘርፍ
    4) በሴቶች ዘርፍ
    5) በወጣቶች ዘርፍ

የቅድመ ምርጫ.... የቀጠለ

1. የፌ/መ/ም/አ/ቦርድ የምርጫ አሰራር አጭር መግለጫ (ማኑዋል) ማዘጋጀት፣
2. የምርጫ ማስፈጸሚያ በጀት ማዘጋጀት፤ ማስጸድቅ እና ስራ ላይ ማዋል፣
3. የየክልል፤ የዞን/ክ/ከተማ፤ የወረዳ እና የመስጅድ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴዎችን በተዋረድ መሰየም::
4. በምርጫ ማኑዋልና መርህግብር ላይ ገለጻና ስልጠና መስጠት
5. የየክልሉ መጅሊስ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ የራሱን ዝርዝር የስራ አፈጻጸም መርህ ግብርና የበጀት ስሌት ተዘጋጅቲ ማጽደቅ::
6. በየወረዳው በሚገኙ መስጂዶች የመስጂድ ጀመኣ አባልነት ምዝገባ መከናወኑን ማረጋገጥ፣

የቅድመ ምርጫ.... የቀጠለ

7. በየወረዳው የሚገኙ መስጂዶችን ቁጥርና ደረጃ መለየት፣ መስጂድ አልባ ወረዳዎችን በመለየት ዝርዝር መረጃዎች ለየእርከኑ አስመራጭ ቦርዱ ማድረስ፣
8. በየመስጂዱ የተመዘገቡ የመስጂድ አባላት የአካባቢው ነዋሪነታቸውና የምዝገባ መስፈርቶችን ማሟላታቸው በማጣራት እርምትና ልዩ የምዝገባ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ፣
9. የእያንዳንዱ ወረዳ መጅሊስ ም/አስፈጻሚ በውስጣቸው የሚገኙ መስጂዶች በሙሉ ለምርጫ አስፈላጊ የሆኑ በጎ ፍቃደኞች፣ የጸጥታ አካላትና መዋቅሮች መኖራቸውን ማረጋገጥ፣
10. በየደረጃው ለሚደረጉ ምርጫዎች የሚያስፈልጉ የገንዘብና የቁሳቁስ ዝግጅቶች መሟላታቸውንና መዳረሳቸውን ማረጋገጥ፣
11. በፌዴራል መጅሊስ የምርጫ ቦርድ አማካኝነት በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ምርጫው የሚከናወንባቸውን ቀናት ማያሳወቅ::

የመራጮች ምዝገባ ሂደትና መስፈርት

1. የመስጅድ አባላት ምዝገባ የሚካሄደው የመስጂድ ምርጫ በጎ ፈቃደኛ ግብረሃል አባላት ይሆናል።

2. ግብረሃይሉ መራጮችን በአምስቱም ዘርፍ ለይቶ በመመዝገብ ለተመዝጋቢዎችም የመራጭነት ካርድ የሚሰጥ ይሆናል።

3. ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ የሆነ ሙስሊም ሁሉ በሚኖርበት ቀበሌ ይሰግድባቸው ከነበሩ መስጂዶች አንዱን መርጦ የነዋሪነት መታወቂያ፤ የመንጃ ፈቃድ፤ የመስሪያ ቤት ወይም የተማሪነት መታወቂያ በማሳየት የመመዝገብ መብት አለው፤

4. በአሳማኝ ምክንያት የነዋሪነት መታወቂያ ያልያዘ ሙስሊም የመስጂዱ ተጠቃሚ መሆኑ በመስጂድ አስተዳደር ወይም የመስጂዱ ተጠቃሚዎች መስካሪነት አስተዳደሩ ሊፈቅድ ይችላል። መስጂዱ ጉዳዩን አጣርቶ ምዝገባውን የሚሠርዝበት በቂ ምክንያት ካገኘ ይሠርዘውና ለወረዳው ሁኔታውን ያስታውቃል።

5. ምዝገባው ክአምስቱ ዘርፎች መካከል ተመዝጋቢው ይበልጥ ይመለከተኛል ብሎ በመረጠው በአንዱ ብቻ ይሆናል።

8.2. የምርጫ ትግበራ ምዕራፍ

8.2.1. በምርጫ እለት ተግባራት

1. የአካባቢው ሁኔታ እንዲሁም የእርከኑ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ ምርጫው ከጠዋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ እስከ ከምሽቱ 12 ሰዓት መጠናቀቅ አለበት።
2. በየእርከኑ በሚደረጉ የምርጫ አካባቢዎች መገኘት ያለባቸው ሰዎች
    1. በመስጅድ ደረጃ ባለው እርከን የመስጅዱ አባሎች፣ ከመስጅድ በላይ ባለው እርከን የጠቅላላ ጉባኤ እጩ አባላት፣
    2. የምርጫ አስፈጻሚዎች፣
    3. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣
    4. ታዛቢዎች፣
    5. የጸጥታ አስከባሪ ሀይሎች፣

8.2.1. የመስጂድ ደረጃ ምርጫ

1. በምርጫ መርሃ ግብሩ በመስጅድ በሚደረገው ምርጫ የመስጅዶች እና የቀበሌ መጅሊስ አመራር ምርጫ ለጊዜው የማይካናወን ይሆናል።

2. ስለዚህ የመጀመሪያ ተመራጮች መስጅድን መነሻ በማድረግ የሚምረጡ የወረዳ መጅሊስ አስትዳደር ተወካዮች ብቻ ይሆናሉ።

3. ስለሆነም የሚደረገው ምርጫው የመስጅድ አስተዳደር ኮሚቴን የማይመለክት ይሆናል።
4. በቂ አባላት የማይገኝበት መስጅድ ማለትም ከአነስተኛው ምድብ (40 መራጮች) በታች የጀመኣ አባላት የያዘ መስጅድ የምርጫ ማእክል አይሆንም።

5. ነገር ግን አባላቱ የመምረጥና የመመረጥ መብታቸው የተጠበቀ ስለሆነ የወርዳዉ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚወስነው ሌላኛው አቅራቢያ መስጂድ ሔደው የሚመዘገቡ ይሆናል።

6. መስጂድ ያልተገነባባቸው አከባቢ ያሉ ሙስሊሞች በሚሰግዱበት ዛውያ፣ቁርኣን ቤት፤መድረሳም ሆነ ዛፍ ስር እንዲመዘገቡ በማድረግ በተመዘገበው የአባላት ብዛት ምድብ የሚስጥ ይሆናል።

የመስጂድ ደረጃ...የቀጠለ

7. የመስጂድ አስመራጭ ኮሚቴ ከወረዳ መጅሊስና ከመስጂድ አመራር አካላት ጋር በመተባበር የመስጂድ ምርጫን ያስተባብራል።

8. የያንዳንዱ መስጅድ ውክልና ቁጥር በመላው ሀገሪቱ በሚደረግ የመራጮች ምዝገባ መጠናቀቅን ተከትሎ በሚደረግ የመረጃ ትንተና በኋላ የሚወሰን ይሆናል።

9. የመስጅድ ምርጫ ለማከናወን መራጮች በየተመዘገቡበት ዘርፍ ከምርጫ ቀን በፊት ባለው የመጨረሻ እሁድ ቀን ከጠዋቱ 3.00 ሰዓት ጀምሮ በመሰባሰብ እንዲተዋወቁ ይደረጋል።

10. በምርጫው እለት ከጠዋቱ 12 ሰኣት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 12 ሰኣት ድረስ በአምስቱም ዘርፎች ለየብቻ በሚደረግ የምርጫ ሂደት አስመራጭ ኮሚቴው መድረኩን እየመራ የሚከናወኑ ተግባራት በሙሉ ቃለ ጉባዔ እንዲያዝ ያደርጋል።

11. በመቀጠል ተሰብሳቢዎች የዘርፉን ሃላፊነት ለመወጣት የተሻለ ብቃት አላቸው ብለው ያሰቡትን አምስት እጩዎችን ከመካከላቸው ይጠቁማሉ።

የመስጂድ ደረጃ...የቀጠለ

15. የእያንዳንዱ እጩ በጠቋሚው ተሰብሳቢ (የመስጂድ አባል) አጭር የህይወት ታሪክ፣ የትምህርት ዝግጅት፣ የስነምግባር ሁኔታው፣ የቀደመ የዲን ኺድማውና በአሁኑ ሰዓት የሚገኝበት የስራ ሁኔታ እንዲገለጽ ይደረጋል።

16. እጩዎች ከተለዩ በኋላ በቅድሚያ መቃወሚያ የሚቀርብበት እጩ ካለ በመለየት በተመራጭነት ይሳተፍ አይሳተፍ የሚለው ላይ ብቻ እጅ በማውጣት ድምጽ እንዲሰጥበት በማድረግ ከተሰብሳቢው ቢያንስ በ1/2ኛ ድምጽ እንዳይሳተፍ የተወሰነበት እጩ ካለ በሌላ እጩ እንዲተካ ይደረጋል።

17. የመስጂድ አስመራጭ ኮሚቴዎች በምዝገባው ሰነድ ላይ በማስፈረም መራጮች ለመስጅድ ተወካዮች ምርጫ የተዘጋጁና በኮሚቴው ሰብሳቢ የተፈረሙ አምስት ካርዶችን (ወረቀቶች) ከተረከቡ በኋላ በቅደም ተከተል የወሰዱትን ካርድ ለመረጡት እጩ ይጥላሉ። ማንበብና መጻፍ ባለመቻላቸው ምክንያት የተመራጮችን ስም ለመለየት ችግር የሚገጥማቸው መራጮች ከተገኙ ምርጫውን ለማስፈፀም በረዳትነት በተመደቡ ግበረ ሀይሎች እንዲታገዙ ይደረጋል። የምርጫ ኮሮጆ ማዳረስ በማይቻልበት አከባቢዎች ላይ እጅ በማውጣት ድምጽ የሚሰጥ የሆናል።

የመስጂድ ደረጃ...የቀጠለ

18. ምርጫው እንደተጠናቀቀ መራጮችና ታዛቢዎች ባሉበት አስመራጭ ኮሚቴው ተራ በተራ ቆጠራ በግልጽ አድርጎ እጩዎችና ያገኙት ድምጽ ዝርዝር ተመዝግቦና ለጉባዔው በግልጽ ተነቦ፤ በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶና በታዛቢዎችና በኮሚቴው እንዲፈረም ይደረጋል

19. የቆጠራው ውጤት የተመዘገበበት የተፈረመው ሠነድ አንዱ ኮፒ ለወረዳው ምርጫ አስፈፃሚ ይላካል።

20. ስለምርጫው ቅሬታ ያለው ሰው በጽሑፍ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ24 ሰዓት ውስጥ ማቅረብ እንደሚችልና ውሳኔም በ48 ሰዓት ውስጥ እንደሚያገኝ ለአባላት ወድያው ይገለፃል።

21. በመጨረሻም ከአንድ እስከ ሶስት ከፍተኛ ድምጽ ያገኙትን የመስጅድ ተመራጮች ስም ዝርዝር ካገኙት ድምጽ ብዛት ጋር በመስጅድ ምርጫ አስፈጻሚ ሰብሳቢ ተፈርሞ ማህተም ተደርጎ በመስጅዱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለህዝብ በሚታይ ቦታ ላይ ይለጣፋል።

8.2.2 የወረዳ አመራር ምርጫ

1. የወረዳ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ መስዶች የየመስጂዱን ምርጫ ውጤት ዝርዝር ሰነዶች ከመስጅድ ምርጫ ቀን በኋላ ቢበዛ 48 ሰዓታት ውስጥ ያሰባስባል።

2. የመስጂድ ምርጫ በተደረገ ቢበዛ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያው ልዩ የወረዳ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ይጠራል።

3. የወረዳ መጅሊስ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ የመስጂድ ምርጫ ውጤቶችን በመተንተን በህገ መጅሊሱ በተቀመጠው የዑለማ ዘርፍ ተመራጮች ድርሻ (ሬሾ) መሰረት (የኡለሞችን ቁጥር ቢያንስ 51% አብላጫ በማስያዝ) ከአምስቱም ዘርፍ ተገቢውን ውክልና ባረጋገጠ መልኩ የወረዳውን ጠቅላላ ጉባዔ ያቋቁማል።

4. ከየመስጂዱ አምስቱን ዘርፎች በወረዳ መጅሊስ ደርጃ እንዲወክሉ የተመረጡት ተወካዮች የወረዳው ኡለማ ም/ቤት ጉባኤ እንዲወክሉ አስመርጦ ከሚልካቸው ዓሊሞች ጋር በመሆን የወረዳው ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ይሆናሉ።

የወረዳ ...ምርጫ የቀጠለ

14. ተመራጭ የወረዳው ሥራ አስፈፃሚ አባላት በእለቱ ከመካከላቸው ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበርና ጸሐፊ በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ (ኮሮጆ) ይመርጣሉ፡፡ ምርጫውን ለማካሄድ ከሚቀርቡ ሁለት ዕጩዎች በቅደም ተከተል ሊቀ መንበር፣ ቀጥሎም ም/ሊቀ መንበሩን ከኡለማዎች መካከል በሚስጢር ይመርጣሉ፡፡ ቀጥሎም ከምሁራን አንድ ፀሓፊ ይመርጣሉ፡፡ ውጤቱ ታዛቢዎች ባሉበት ተቆጥሮ ውሳኔው ይመዘገባል፡፡

15. በመቀጠል ከሁሉም ዘርፍ በጋራ በሚደረግ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሳባ ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል በሁሉም አባላት ጠቋሚነትና መራጭነት ሶስት የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አባላት በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ (ኮሮጆ) ይመረጣሉ፡፡

16. አስመራጭ ኮሚቴው የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አባላትና የስራ አስፈጻሚውን ሶስት አመራሮች ምርጫ ድምጽ ቆጠራ ውጤት እዛው በማሳወቅና በመመዝገብ ለቀጣይ እርከን ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከእለቱ ቃለ ጉባዔ ጋር ያስተላልፋል፡፡

የዞን/ክፍለ ከተማ አመራር ምርጫ

1. የዞን/ክ/ከተማ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ በዞኑ/ክ/ከተማው ውስጥ ከሚገኙ የወረዳ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች የየወረዳውን ምርጫ ውጤት ዝርዝር ሰነዶች ከምርጫው ቀን በኋላ ቢበዛ 48 ሰዓታት ውስጥ ያሰባስባል።

2. በመቀጠልም የወረዳ ምርጫ በተጠናቀቀ ቢበዛ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያው ልዩ የዞን/ክ/ከተማ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ይጠራል።

3. የዞን/ክ/ከተማ መጅሊስ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ የወረዳዎችን ምርጫ ውጤቶች በመተንተን በህገ መጅሊሱ በተቀመጠው የዑለማ ዘርፍ ተመራጮች ድርሻ (ሬሾ) መሰረት (የኡለሞችን ቁጥር ቢያንስ 51% አብላጫ በማስያዝ) ከአምስቱም ዘርፍ ተገቢውን ውክልና ባረጋገጠ መልኩ የዞን/ክ/ከተማን ጠቅላላ ጉባዔ ያቋቁማል።

የዞን/ክፍለ ከተማ...የቀጠለ

8. በመቀጠል የየዘርፉ ሊቀመንበር፤ ም/ሊቀመንበር ና ጸሃፊ በዘርፉ አባላት ብቻ በሚደረግ መራጭነት ለእያንዳንዳቸው በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ (ኮሮጆ) ድምጽ እንዲሰጥ ይደረጋል።

9. ኮሚቴው የየዘርፍ ተመራጮች ድምጽ አሰጣጥ ስነስርዓት እንደተጠናቀቀ የቆጠራውን ውጤት እዛው በመድረክ ላይ ለዘርፉ አባላት በማሳወቅ በቃለ ጉባኤ ይመዘግባል።

10. የአምስቱ ዘርፍ ሊቃነ መናብርትና በዞን/ክ/ከተማ ኡለሞች ጉባኤ ተወክለው በዘርፉ ዓሊሞች የሚመረጡ አራት ተጨማሪ ዓሊም ተወካዮች የዞኑ/ክ/ከተማው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናሉ።

11. የዞኑ/ክ/ከተማው ሥራ አስፈፃሚ አባላት በእለቱ ከመካከላቸው ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበርና ጸሐፊ በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ (ኮሮጆ) ይመርጣሉ። ምርጫውን ለማካሄድ ከሚቀርቡ ሁለት ዕጩዎች በቅደም ተከተል ሊቀ መንበር፣ ቅጥሎም ም/ሊቀ መንበሩን ከኡለማዎች መካከል በሚስጢር ይመርጣሉ። ቀጥሎም ከምሁራን አንድ ፀሓፊ ይመርጣሉ። ውጤቱ ታዛቢዎች ባሉበት ተቆጥሮ ውሳኔው ይመዘገባል።

የዞን/ክፍለ ከተማ አመራር ምርጫ

1. የዞን/ክ/ከተማ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ በዞኑ/ክ/ከተማው ውስጥ ከሚገኙ የወረዳ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች የየወረዳውን ምርጫ ውጤት ዝርዝር ሰነዶች ከምርጫው ቀን በኋላ ቢበዛ 48 ሰዓታት ውስጥ ያሰባስባል።

2. በመቀጠልም የወረዳ ምርጫ በተጠናቀቀ ቢበዛ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የመጀመሪያው ልዩ የዞን/ክ/ከተማ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ይጠራል።

3. የዞን/ክ/ከተማ መጅሊስ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ የወረዳዎችን ምርጫ ውጤቶች በመተንተን በህገ መጅሊሱ በተቀመጠው የዑለማ ዘርፍ ተመራጮች ድርሻ (ሬሾ) መሰረት (የኡለሞችን ቁጥር ቢያንስ 51% አብላጫ በማስያዝ) ከአምስቱም ዘርፍ ተገቢውን ውክልና ባረጋገጠ መልኩ የዞን/ክ/ከተማን ጠቅላላ ጉባዔ ያቋቁማል።

የዞን/ክፍለ ከተማ...የቀጠለ

4. ከየወረዳው የተመረጡ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትና በዞኑ/ክ/ከተማው የዓሊሞች ጉበኤ ተመርጠው የሚወከሉት አባላት በጋራ የዞኑ/ክፍለ ከተማው ጠቅላላ ጉባኤ አባል ይሆናሉ።

5. የዞን/ክ/ከተማ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከስብሰባው እለት በፊት ለዕለቱ ምርጫ የሚያስፈልጉ የኮሮጆ፣ እስክሪፕቶና ወረቀት እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶች የማሟላት ስራ ያከናውናል።

6. የመጀመሪያው የዞን/ክ/ከተማ መጅሊስ ጠቅላላ ጉባዔ የሚመራው በዞን/ክ/ከተማ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲሆን ኮሚቴው በእለቱ የራሱን ሰብሳቢና ጸሐፊውን ከኮሚቴው አባላት መካከል ይመርጣል።

7. የመጀመሪያው ልዩ የዞን/ክ/ከተማ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ የሚሆነው 1ኛ) የዞን/ክ/ከተማ መጅሊስ ስራ አስፈጻሚዎች ምርጫ፤ 2ኛ) የዞን/ክ/ከተማ መጅሊስ ስራ አስፈጻሚ አመራር ምርጫና 3ኛ) የኢዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አባላትን ምርጫ ብቻ ይሆናል።

የዞን/ክፍለ ከተማ...የቀጠለ

14. ምርጫው በሚስጢራዊ ሁኔታ በጽሑፍ ይደረጋል፡፡ ምርጫው እንደተጠናቀቀም ታዛቢዎችና መራጮች ባሉበት ይቆጠራል፡፡ በምርጫ አስፈፃሚውና ታዛቢዎች በሁለት ገጽ ተዘጋጅቶ ይፈረማል፡፡ አስመራጭ ኮሚቴው የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አባላትና የስራ አስፈጻሚውን ሶስት አመራሮች ምርጫ ድምጽ ቆጠራ ውጤት እዛው በማሳወቅና በመመዝገብ ለቀጣይ እርከን ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከእለቱ ቃለ ጉባዔ ጋር ያስተላልፋል፡፡

15. ከዘርፎች ተመርጦ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆነ አባል ተወክሎ በሄደበት ላይኛው እርከን እንደ ገና በመመረጡ ምክንያት ይዞት የነበረው የታች ቦታው ክፍት ከሆነ የዘርፉ አባላት ተሰብስበው ምትኩን መርጠው ይወክላሉ፡፡

የክልል/ የከተማ... የቀጠለ

1.የአምስቱ ዘርፍ ሊቃነ መናብርትና በክልል/ከተማ ኡለሞች ጉባኤ ተወክለው በዘርፉ ዓሊሞች የሚመረጡ አራት ተጨማሪ ዓሊም ተወካዮች የክልሉ/ከተማው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናሉ።

2.የክልሉ/ከተማው ሥራ አስፈፃሚ አባላት በእለቱ ከመካከላቸው ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበርና ጸሐፊ በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ (ኮሮጆ) ይመርጣሉ። ምርጫውን ለማካሄድ ከሚቀርቡ ሁለት ዕጩዎች በቅደም ተከተል ሊቀ መንበር፣ ቅጥሎም ም/ሊቀ መንበሩን ከኡለማዎች መካከል በሚስጢር ይመርጣሉ። ቀጥሎም ከምሁራን አንድ ፀሓፊ ይመርጣሉ። ውጤቱ ታዛቢዎች ባሉበት ተቆጥሮ ውሳኔው ይመዘገባል።

3.በመቀጠል ከሁሉም ዘርፍ በጋራ በሚደረግ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሳባ ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት መካከል በሁሉም አባላት ጠቋሚነትና መራጭነት አምስት የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አባላት በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ (ኮሮጆ) ይመረጣሉ።

4.የጠቅላላ ጉባዔው አባላት በየዘርፋቸው ተሰባስበው እንዲተዋወቁ ይደረጋል። ለክፍለ ከተማው የዘርፉቸው ሊቀ መንበር፣ ምክትል ሊቀ መንበርና ፀሓፊ ለመሆን ከፍተኛ ብቃትና ዝገጅት ያለቸውን ለመምረጥ የህይወት ታሪካቸውን አስመልክቶ ገለፃ ይደረጋል። በይበልጥም ጠቋሚዎች ስለሚጠቁሙት ሰው ማንነት በቂ ገለፃ እንዲሰጡ ዕድል ይሰጣል።

የፌደራል መጅሊስ ም/ቤት አመራሮች ምርጫ

1. የፌዴራል መጅሊስ ምርጫ አስፈጻሚ ቦርድ የየክልልና ሁለቱ ከተማ አስተዳደር መጅሊስ ምርጫ እንደተጠናቀቀ ቢበዛ በአንድ ሳምንት ውስጥ ከክልል እና ሁለቱ ከተማ አስተዳደር መጅሊስ ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ዝርዝር የምርጫ ውጤት ሰነዶች አሰባስቦ ያጠናቅቃል።
2. የየክልልና ሁለቱ ከተማ አስተዳደር መጅሊስ ምርጫ ውጤቶችንና የኡለማ ም/ቤት ኮታ ሹመት ውሳኔዎችን በመተንተን በተቀመጠው የዑለማ ተመራጭ ድልድል (Ratio)ና የክልሎች ኮታ መሰረት የጠቅላይ ም/ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ ይቋቋማል።
3. የሚቋቋመው የፌደራል መጅሊስ ጠ/ጉባኤ 195 ተወካዮችን በማያዝ በሚከተሉት ኮታ መሰረት የሚዋቀር ይሆናል።
4. የየክልሉና ሁለቱ ከተማ አስተዳደር መጅሊስ 3 አመራር (ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ፀሐፊ) እና 2 ተጨማሪ አባላት፤

- በድምሩ (3x14) + (2x14) = 70 ተወካዮች

የተጠቃለለ(summary) የምርጫ አይነቶች በየእርከን

የምርጫ አይነቶች	በየጅሊስ አስተዳደር እርከን የሚከናወኑ የምርጫዎች				
	የመስጂድ የዘርፍ አመራር ምርጫ	የወረዳ/የቀበሌ የዘርፍ አመራር ምርጫ	የክፍለ ከተማ /የዞን አመራር ምርጫ	የክልል / የከተማ አስተዳደር ምርጫ	የጠቅላይ ምክር ቤት አ ምርጫ
	በመስጅድ በሚደረገው የመስጂድ አመራር ምርጫ ደርጃ ምርጫ ለጊዜው የማይካናወን	• በወረዳው ስር ከሚገኙ መስጅዶች የየዘርፉ ተወካዮች እና • የወረዳው ኡለማ ም/ቤት (አመራር) አባላት በሙሉ	• ከየወረዳው የተመረጡ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣ • የዞኑ/ክ/ከተ·ማ ኡለማ (አመራር) ም/ቤት· አባላት· በሙ·ሉ	• ከየዞኑ/ ከየክፍለ ከተ·ማው የተመረጡ ሥራ አስፈ·ፃሚ አባላት· • የክልሉ/ከተ·ማ አስተዳደሩ ኡለማ ም/ቤት·(አመራር) አባላት· በመ·ሉ	የየክልሉ·ና ሁለቱ ከተ·ማ መጅሊስ ም/ፕ ምክትል ፕሬዚዳንትና 2 ተጨማሪ አባላት ከአ በጥቅሉ (3*14) + (2*1 ተወካዮች
		ምሳሌ፦ በወረዳው 10 መስጅዶች ቢኖሩ የወረዳው ጠ/ጉባኤ አባላት የሚ የከትተው፦	ምሳሌ- በክ/ከተማው/ዞኑ 5 ወረዳዎች ቢኖሩ የጠ/ጉባአኤ ብዛት = (9x5) +የዞኑ/ክ/ከተማ ኡለማ ም/ቤት (አመራር)	ምሳሌ- በክልሉ 10 ዞኖች ቢኖሩ የጠ/ጉባኤ አባላት ብዛት = (10x9) + የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ኡለማ ም/ቤት	ከፍተኛ ሕዝበ ሙስሊም 6 ክልሎች ተጨማሪ አ 1) ከኦሮሚያ ክልል 2(2) ከሶማሌ ክልል 8 አ 3) ከአማራ ክልል 8 አ 4) ከማአከላዊ ኢ/ክልል 5) ከአፋር ተጨማሪ 4

የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ምርጫ	... ሂሂሷ ሷዜኅ አመራር ምርጫ ለጊዜው የማይካናወን ሲሆን መስጅዶች የላይኛውን እርከን የቀበሌ / ወረዳ መጅሊስ አስትዳደር ተወካዮችን ለመምረጥ እንደ ምርጫ ጣቢያነት የሚያገለግሉ ይሆናል	ቢኖሩ የወረዳው ጠ/ጉባኤ አባላት የሚያካትተው፡- = (ከየመስጅዱ የሚመረጡ የወረዳ የ 5ቱ ዘርፍ ተወካይ አባላት ብዛት x10 መስጅዶች)+ የወረዳዉ ኡለማ ም/ቤት (አመራር) አባላት በሙሉ የየመስጅድ የወረዳ ተወካዮች ከታ/ ብዛት በመላ ሀገሪቱ በየወረዳው ያሉ የመስጂዶች በዛት መረጃ ከተሰባሰበ በኋላ በቦርዱ የሚወሰን ይሆናል።	የጠ/ጉባኤ ብዛት = (9x5) +የዞኑ/ክ/ከተማ ኡለማ ም/ቤት (አምራር) አባላት በሙሉ	የጠ/ጉባኤ አባላት ብዛት = (10x9) + የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ኡለማ ም/ቤት (አምራር) አባላት በሙሉ	3) ከአማራ ክልል 8 አባላት፣ 4) ከማአከላዊ ኢ/ክልል 4 አባላት፣ 5) ከአፋር ተጨማሪ 4 አባላት፣ 6) ከአ/አ ከተማ አስተዳድር 2 አባላት **በጥቅሉ** 46 ሀ.ከኦሮሚያና ከአዲስ አበባ አራት አራ... ተወካዮች፣ ከተቀሩት 12 ክልሎ... ከያንዳንዱ ሁለት ሁለት የሚወክ... **በድምሩ 32 ምሁራን ተወካዮች፣** ለ.ከየክልሉና ከተማ አስተዳደሩ (በድም... 42 አባላት)፡ • የንግድና የሌሎች ሙ.ያ ማ/ሰ... አደረጃጀቶች የሚመረጡ አንዳን... **በድምሩ 14 ተወካዮች፣** • የወጣት አደረጃጀት አባላ... የሚመረጡ አንዳንድ **በድምሩ** ... **ተወካዮች** • የሴቶች አደረጃጀቶች የሚመረ... አንዳንድ **በድምሩ 14 ተወካዮች** በአምስቱ አህጉራት ዲያስፖራ ኢትዮጵ...

					ሙ·ስሊሞት የሚወከሉ አንዳንድ አባላት በድምሩ 5 አባላት 70+46+32+42+ 5 = 195
የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምርጫ	- 5ቱ የወረዳው የየዘርፍ ሊቃነ መናብርት - በዓሊሞች ጉባኤ የሚወከሉ ተጨማሪ 4 የኡለማ ተወካዮች = 5+4 = 9 **የስራ አስፈጻሚ አባላት** ይሆናሉ	5ቱ የየዘርፉ ሊቃነ መናብርት 4 በወረዳው ዓሊሞች ዘርፍ ተመርጠው የሚወከሉ **ጠቅላላ የስራ አስፈጻሚ ብዛት = 9 አባላት ናቸው**	5ቱ የየዘርፍ ሊቃነ መናብርትና የክልሉ ዓሊሞች ዘርፍ መርጦ የሚወክላቸው አራት ዓሊሞች በጋራ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይመሠርታሉ **ጠቅላላ የስራ አስፈጻሚ ብዛት = 9 የሆናሉ**	• ከኡለማ ዘርፍ አባላት ለሥራ አስፈፃሚ አባልነት የተቀመጡ መሥፈርቶችን ከሚያሟሉ ከፍተኛ ዓሊሞች መካከል 18 ዕጩዎችን ተዘጋጅተው፣ ለጠቅላላ ጉባኤው በማቀረብ 10 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ይመረጣሉ፣ • የቀሩት አራት ዘርፍ አባላት በጋራ ተሰብስበው ለሥራ አስፈፃሚነት 15 ዕጩዎች ተዘጋጅተው፣ ለጠቅላላ ጉባኤውም በማቅረብ 5 የሥራ አስፈፃሚ አባላት ይመረጣል ጠ/ም/ቤቱ በድምሩ 15 የስራ አስፈጻሚ አባላት ይኖሩታል
የስራ አስፈጻሚ አመራር ኮሚቴ	• የወረዳ መጅሊስ ሊቀመንበር እና ም/ሊቀ/መንበር አመራር ከኡለሞች መካከል የሚመረጡ ይሆናል	• ከዓሊሞች ዘርፍ የሊቀ መንበርና የም/ሊቀ መንበር ጥቆማዎች ተየርጎ ከማቱ በተራ	• ከዓሊሞች ዘርፍ የሊቀ መንበርና የም/ሊቀ መንበር ጥቆማዎች ተየርጎ ከማቱ በተራ	ሥራ አስፈፃሚ አባላት በስብሰባ የጉባኤውን ፕሬዚዳንት፣ ተቀዳሚ ም/ፕሬዚዳንትንና ምክትል ፕሬዝዳን· ከዓሊሞች መካከል፣ ዋና ጸሓፊን	

በየጅሊስ አስተዳደር እርከን የሚከናወኑ የምርጫዎች

ሞርጫ አይነቶች	የመስጂድ የዘርፍ አመራር ምርጫ	የወረዳ/የቀበሌ የዘርፍ አመራር ምርጫ	የክፍለ ከተማ /የዞን አመራር ምርጫ	የክልል / የከተማ አስተዳደር ምርጫ	የጠቅላይ ምክር ቤት አስተዳደር ምርጫ
የጠቅላላ ጉባኤ አባላት	በመስጅድ በሚደረገው ምርጫ የመስጂድ ደርጃ አመራር ምርጫ ለጊዜው የማይካናወን ሲሆን መስጅዶች የላይኛውን እርከን የቀበሌ / ወረዳ	• በወረዳው ስር ከሚገኙ መስጅዶች የየዘርፉ ተወካዮች እና • የወረዳው ኡለማ ም/ቤት (አመራር) አባላት በሙሉ ምሳሌ፡- በወረዳው 10 መስጅዶች ቢኖሩ የወረዳው ጠ/ጉባኤ አባላት የሚያካትተው፡- = (ከየመስጅዱ የሚመረጡ የወረዳ የ 5ቱ ዘርፍ ተወካይ አባላት	• **ከየወረዳው የተመረጡ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣** • የዞን/ክ/ከተማ ኡለማ (አመራር) ም/ቤት አባላት በሙሉ ምሳሌ- በክ/ከተማው/ዞኑ 5 ወረዳዎች ቢኖሩ የጠ/ጉባኤ ብዛት = (9x5) +የዞን/ክ/ከተማ ኡለማ ም/ቤት (አምራር) አባላት በሙሉ	• ከየዞኑ/ ከየክፍለ ከተማው የተመረጡ ሥራ አስፈፃሚ አባላት • የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ኡለማ ም/ቤት(አመራር) አባላት በሙሉ ምሳሌ- በክልሉ 10 ዞኖች ቢኖሩ የጠ/ጉባኤ አባላት ብዛት = (10x9) + የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ኡለማ ም/ቤት (አምራር) አባላት በሙሉ	የየክልሉና ሁለቱ ከተማ አስተዳደር መጅሊስ 3 አመራር /ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ፀሐፊ/ እና 2 ተጨማሪ አባላት ከኡለማ መከከል **በጥቅሉ (3*14) + (2*14)= 70 ተወካዮች** ከፍተኛ ሕዝበ ሙስሊም ካሚገኝባቸው 6 ክልሎች ተጨማሪ አባላት ኮታ 1) ከኦሮሚያ ክልል 20 አባላት፣ 2) ከሶማሌ ክልል 8 አባላት፣ 3) ከአማራ ክልል 8 አባላት፣ 4) ከማአከላዊ ኢ/ክልል 4 አባላት፣ 5) ከአፋር ተጨማሪ 4 አባላት፣ 6) ከአ/አ ከተማ አስተዳድር 2 አባላት **በጥቅሉ** 46 ሀ.ከኦሮሚያና ከአዲስ አበባ አራት አራ ተወካዮች፣ ከተቀሩት 12 ክልሎ

በየጅሊስ አስተዳደር እርከን የሚከናወኑ የምርጫዎች

ስጂድ የዘርፍ ራር ምርጫ	የወረዳ/የቀበሌ የዘርፍ አመራር ምርጫ	የክፍለ ከተማ /የዞን አመራር ምርጫ	የክልል / የከተማ አስተዳደር ምርጫ	የጠቅላይ ምክር ቤት አስተዳደር ምርጫ
	• በወረዳው ስር ከሚገኙ መስጅዶች የየዘርፉ ተወካዮች እና • የወረዳው ኡለማ ም/ቤት (አመራር) አባላት በሙሉ	• **ከየወረዳው የተመረጡ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣** • የዞኑ/ክ/ከተማ ኡለማ (አመራር) ም/ቤት አባላት በሙሉ	• ከየዞኑ/ ከየክፍለ ከተማው የተመረጡ ሥራ አስፈፃሚ አባላት • የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ኡለማ ም/ቤት(አመራር) አባላት በሙሉ	የየክልሉና ሁለቱ ከተማ አስተዳደር መጅሊስ 3 አመራር /ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ፀሐፊ/ እና 2 ተጨማሪ አባላት ከኡለማ መከከል **በጥቅሉ (3*14) + (2*14)= 70 ተወካዮች**
ስጅድ ሚደረገው ርጫ የመስጂድ ጂ አመራር ምርጫ ዚው የማይካናወን ያን መስጅዶች ይኛውን እርከን በሌ / ወረዳ ጅሊስ አስትዳደር	ምሳሌ፦ በወረዳው 10 መስጅዶች ቢኖሩ የወረዳው ጠ/ጉባኤ አባላት የሚያካትተው፦ = (ከየመስጅዱ የሚመረጡ የወረዳ የ 5ቱ ዘርፍ ተወካይ አባላት	ምሳሌ- በክ/ከተማው/ዞኑ 5 ወረዳዎች ቢኖሩ የጠ/ጉባኤ አባላት ብዛት = (9x5) +የዞኑ/ክ/ከተማ ኡለማ ም/ቤት (አምራር) አባላት በሙሉ	ምሳሌ- በክልሉ 10 ዞኖች ቢኖሩ የጠ/ጉባኤ አባላት ብዛት = (10x9) + የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ኡለማ ም/ቤት (አምራር) አባላት በሙሉ	ከፍተኛ ሕዝበ ሙስሊም ከሚገኝባቸው 6 ክልሎች ተጨማሪ አባላት ከታ 1) ከኦሮሚያ ክልል 20 አባላት፣ 2) ከሶማሌ ክልል 8 አባላት፣ 3) ከአማራ ክልል 8 አባላት፣ 4) ከማአከላዊ ኢ/ክልል 4 አባላት፣ 5) ከአፋር ተጨማሪ 4 አባላት፣ 6) ከአ/አ ከተማ አስተዳድር 2 አባላት **በጥቅሉ** 46
				ሀ.ከኦሮሚያና ከአዲስ አበባ አራት አራት ተወካዮች፣ ከተቀሩት 12 ክልሎች

በየጅሊስ አስተዳደር እርከን የሚከናወኑ የምርጫዎች

ᵒስጂድ የዘርፍ ᵓራር ምርጫ	የወረዳ/የቀበሌ የዘርፍ አመራር ምርጫ	የክፍለ ከተማ /የዞን አመራር ምርጫ	የክልል / የከተማ አስተዳደር ምርጫ	የጠቅላይ ምክር ቤት አስተዳደር ምርጫ
	• በወረዳው ስር ከሚገኙ መስጅዶች የየዘርፉ ተወካዮች እና • የወረዳው ኡለማ ም/ቤት (አመራር) አባላት በሙሉ	• **ከየወረዳው የተመረጡ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣** • የዞኑ/ክ/ከተማ ኡለማ (አመራር) ም/ቤት አባላት በሙሉ	• ከየዞኑ/ ከየክፍለ ከተማው የተመረጡ ሥራ አስፈፃሚ አባላት • የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ኡለማ ም/ቤት(አመራር) አባላት በሙሉ	የየክልሉና ሁለቱ ከተማ አስተዳደር መጅሊስ 3 አመራር /ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንትና ፀሐፊ/ እና 2 ተጨማሪ አባላት ከኡለማ መከከል **በጥቅሉ (3*14) + (2*14)= 70 ተወካዮች**
ᵒስጅድ ሚደረገው ᵓጫ የመስጂድ ᵓጃ አመራር ምርጫ ዜው የማይካናወን ᵽን መስጅዶች ይኛውን እርከን በሌ / ወረዳ ጅሊስ አስትዳደር	ምሳሌ፦ በወረዳው 10 መስጅዶች ቢኖሩ የወረዳው ጠ/ጉባኤ አባላት የሚያካትተው፦ = (ከየመስጅዳ የሚመረጡ የወረዳ የ 5ቱ ዘርፍ ተወካይ አባላት	ምሳሌ- በክ/ከተማው/ዞኑ 5 ወረዳዎች ቢኖሩ የጠ/ጉባኤ ብዛት = (9x5) +የዞኑ/ክ/ከተማ ኡለማ ም/ቤት (አምራር) አባላት በሙሉ	ምሳሌ- በክልሉ 10 ዞኖች ቢኖሩ የጠ/ጉባኤ አባላት ብዛት = (10x9) + የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ኡለማ ም/ቤት (አምራር) አባላት በሙሉ	ከፍተኛ ሕገበ ሙስሊም ከሚገኝባቸው 6 ክልሎች ተጨማሪ አባላት ኮታ 1) ከኦሮሚያ ክልል 20 አባላት፣ 2) ከሶማሌ ክልል 8 አባላት፣ 3) ከአማራ ክልል 8 አባላት፣ 4) ከማአከላዊ ኢ/ክልል 4 አባላት፣ 5) ከአፋር ተጨማሪ 4 አባላት፣ 6) ከአ/አ ከተማ አስተዳድር 2 አባላት **በጥቅሉ** 46
				ሀ.ከኦሮሚያና ከአዲስ አበባ አራት አራት ተወካዮች፣ ከተቀሩት 12 ክልሎች

የፌደራል መጅሊስ አመራር አባለት ውክልና ቀመር

የፌደራል ጠ/ጉባኤ አባላት 195	116 ኡለማ (65%)	ከ14ቱ ክልሎች (42)	3 የስራ አስፈጻሚ አባላት	42
		ከ14ቱ ክልሎች (28)	2 ተጨማሪ ከየክልል	28
		ከ85% በላይ የሀገራችንን ሙስሊሞች ከሚወክሉ 6 ክልሎች (46)		
			ከኦሮሚያ	20
			ከሶማሌ	8
			ከአማራ	8
			ከማእከላዊ ኢትዮጵያ	4
			ከአፋር	4
			ከአዲስ አበባ	2
				116
	79 ከሌሎች (35%)	ከምሁራን	አዲስ አበባ	4
			ኦሮሚያ	4
			የተቀሩት 12 ክልሎች	24
		ከንግድና ልዩ ልዩ ሙያተኞች ክፍል	ለያንዳንዱ ክልል 1 ተወካይ	14
		ከሴቶች አደረጃጀት	ለያንዳንዱ ክልል 1 ተወካይ	14
		ከወጣቶች አደረጃጀት	ለያንዳንዱ ክልል 1 ተወካይ	14
		የዳያስፖራ ሙስሊም ተወካዮች	ለየአህጉር 1ተወካይ	5
				79
የፌደራል ስራ አስፈጻሚ አባላት 15	10 ኡለማኦች (67%) 5 ምሁራኖች (33%)			
		ከኦሮሚያ		2
		ከሁሉም ክልሎች አንዳንድ ተወካይ		13
				15